# ምስጋና ለ”ስም-የለሽ”

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)

እኔ እስከማውቀው ድረስ አለምን ከዳር እስከ ዳር በአንዴ ያገናኘ እንደ ዘንድሮው ያለ የአሜርካ ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ በአለም ላይ ነበረ ብዬ ማመን ያስቸግረኛል። የሙሴ፣ የእየሱስ ክርስቶስ፣ የመሐመድ ወይም የቡድሃ ምጣት እንኳን የአቶ ኦባማን ያህል ድፍን አለምን በቅጽበት ውስጥ ያዳረሰ አይመስለኝም። ከልጅነት ጀምሮ ያዳበሩት እውቀት፣ የአመራር ችሎታቸውና በሰብአዊነት ሥነ-ምግባር የተሞላው ባህሪያቸው በእርግጥም ይገባቸዋል፣ ይበል፣ ይሁን ያሰኛቸዋል። ነገር ግን አቶ ኦባማ ለዚህ ደረጃ የደረሱት ስንት ነፍሶች በምድር ላይ መከራቸውን አይተውና ተሰቃይተው፣ ስንት ህይወቶች ባርነትን በመቃወማቸው በለጋ እድሜአቸው ተጎሳቁለውና ተቀጭተው መሆኑ አይካድም። አቶ ኦባማ በተወለዱበት ዘመን የነበረው የአሜርካ ሁኔታ እንዳለ ቢቆያቸውማ ኖሮ፤ ዛሬ እንኳን ፕሬዘዳንት ሊሆኑ የምርጫ ካርድ ተሰጥቷቸው ወደ ምርጫ ጣቢያ መሄድም ባልቻሉ ነበር።

በቅዱሱ የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንክ ገላ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ስማቸው ሳይጣፍ በቀሩት ነገር ግን በየጥሻው አረመኔዎችንና ኢሰብአዊነትን ሲታገሉ በወደቁት የሰው ልጆች አጥንትና ስጋ በዳበረው እርሻ ላይ ብሩሁ አቶ ኦባማ አድገው፣ አብበውና አፍርተው ነጩን ቤተ-መንግስት ለጊዜውም ቢሆን ወደ ጥቁርነት ቀይረውታል። እንደኔ እንደኔ ለአቶ ኦባማ ወንበር እግሮችም ሆነ ለእኛ ለስደተኞች የአሜሪካ እንጀራ ሞሰቦች እነዚያ ዛሬ ስማቸው ብዙም የማይታወቀው ነገር ግን ከሆዳቸው መንፈሳቸውን አስቀድመው ባርነትን በመታገል ህይወታቸውን ያጡት ከሰውም በላይ ሰው የሆኑ ዛሬ ስማቸውን የማናውቃቸውና የማናነሳቸው ወይም የዘነጋናቸው “ስም-የለሽ” ሰዎች ናቸው።

በእድሜ ጦቢያ ከአሜሪካ ቢያንስ ቢያንስ በአስር እጅ ትበልጣለች። እንደ ወግ ማእረጉ ቢሆንማ ኖሮ ጦቢያ በእድሜ ባለጸጋነቷ አሜሪካን በስልጣኔ አስከንድታ ቀድማ መንገድ ማሳየትና መምራት እንደዚሁም ለአለም አርአያ መሆን መቻል ነበረባት። ይህን ስል በአንዳዶቻችሁ አእምሮ ውስጥ “ጽድቁ ቀርቶ በአግባቡ በኮነነኝ” የሚለው ተረት ሊመጣባችሁ እንደሚችል እገምታለሁ። ዛሬ የአለም ሕዝብ አንድ እየሆነ በመጣበት በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን፣ በዚህ የጥቁርንና የነጭን ድንበር እንኳን ለማጥፋት እቅድ በወጣበት ዘመን፤ በቅኝ አገዛዞች ከንቱ የመንፈስ ሸንት ተላቁጦና ተቦክቶ የተሰራ ጭንላት ባለቸው ገዥዎች ምክንያት፤ በቤተ-ሙከራ ምርምር እንኳ ሊለዩ የማችሉት ወንድምና እትማማቾች አገር የሆነችው ጦቢያ በዘር ተከፋፍላ እየተናቆረች ራሷን በራሷ ስታደማ ትውላለች።

ድሮ በዚህ በውጩ አለም ባሮቻቸውን ከግንድ ጋር እያሰሩ እንደሚገርፉት፣ ከአውሬ ጋር እያፋለሙ እንደሚዝናኑት የባርያ ጌታዎች፤ ሳይፈለጉ ወንበር ላይ ቁጢጥ ያሉ የጦቢያ ገዥዎችም ለጥ ገጥ ብሎ ያልተገዛውን ዜጋ ከስራ ያባርሩታል፣ ንብረቱን ይቀሙታል፣ ያሰድዱታል፣ እግር ከወርች ያስሩታል፣ ይገርፉታል፣ እንዲያም ሲል እንደ ቆሌ ጠቦት ይሰውታል። ታዲያ በእንደዚህ አይነቱ አሰቃቂ የታሪክ ሂደት ወቅት አንዳንዶቻችን የዚህ ግፍ ፈጻሚቾች አገልጋይና እንባ ጠባቂ ሆነን እናገለግላለን። ብዙዎቻችንም ሌሎች (ስም-የለሾች) ደማቸውን አፍሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው የተሻለ ቀን እስኪያመጡልን ድረስ አድፍጠን እንጠብቃለን። ግፍ መቀበልና ማየት አንገፍግፍናል የምንል አንዳንዶቻችን ደግሞ ብዕር እናነሳለን ወይም የመፈክር ሰሌዳ ይዘን አደባባይ እንወጣለን። ከዚህ ከመጨረሻው ቡድን የምንመደበው እንኳን ብዙውን ጊዜ የምንጮኸው የታወቀ ምሁር፣ የፖለቲካ መሪ፣ የወጣለት ዘፋኝ ወይም ሯጭ ወዘተርፈ መከራ ሲደርስበት ብቻ ነው።

ዳሩ ግን ቻጋር፣ በሽታና ግፍ ሳያባራ እንደዝናብ በሚዘንብባት ኢትዮጵያ በአያሌው አካላዊና መንፈሳዊ ግፍ የሚፈጸምባቸው ጋዜጣ፣ ሬድዮ ወይም ቴለቪዥን ላይ ስማቸው ወይም ምስላቸው የማይወጣ፤ ስም እያላቸው ስም-የለሽ የሆኑ ዜጎች ናቸው። ጋዜጣ በማዞሩ መንገድ ዳር ጫማ እንዳይጠርግ የሚከለከለውን ጫማ ጠራጊ እርሱ ይቁጠረው። አደገኛ ቦዘኔ እየተባለ የጥይት ራትና ምሳ፣ በወህኒ ቤት የቁንጫ፣ የትኋንና የበሽታዎች ቀለብ የሚሆነውን ዜጋ ብዛት የምታውቀው ወላጅቱ ጦቢያና አምላክ ናቸው። ከገዥዎች ጎን አብሮ ባለመሰልፉ ከስራ የሚባረረውን ወይም የሚሰደደውን አለዚያም የሚገደለውን አስተማሪም ሆነ ሌላ ሰርቶ-አዳሪ ብዛት የሚያውቁት በችጋር የሚማቅቁት ቤተሰቦቻቸውና እግዜአብሄር ናቸው። ለአገዛዙ ባለመስገዱ መሬቱን የሚቀማውን፣ ማዳበርያ የሚከለከለውንና በየጥሻው የሚወድቀውን ገበሬ ብዛት የሚያውቁት የጦቢ ምድርና አላህ ናቸው። ለእንደዚህ አይነቱ ግፍ እንግዳ ስላልሆናችሁ እዚህ ላይ ልተወው እንጅ ሰቆቃው ተዘርዝሮ አያልቅም።

በአሜሪካን አገር እነ ማርቲን ሉተር ኪንግና እነ ስም-የለሽ ለጎበዙ አቶ ኦባማ የስልጣን መሰላል፣ ለቀሪው የጥቁርና ሌላም ዜጋ የተስፋ ምንጭ፣ ለእንደኛ አይነቱ ስደተኛ ደግሞ የእንጀራ መበያ ሞሰብ ሆነዋል። በእኛም አገር በጥቂቶቹ ስም

በተሰጣቸው ጀግኖችና ብዛት ባላቸው ነገር ግን ስማቸው ባልተጻፈና በተረሱ ስም-የለሽ አንበሶች መስዋእትነት ምክንያት ቅኝ አገዛዝ ከሚባል አሰልስል በሽታ ተገላግለን ኖረናል። ዛሬም የጥንቱን የቅኝ ገዥዎችን እቅድና ንድፍ ለመፈጸም ሲኳትኑ ከሚታዩት የቅኝ-ተገዥ ገዥዎች ሊያላቅቁን እስከ ህልፈተ-ሕይወት ድረስ መከራና ስቃይን ሲቀበሉ የሚውሉት እነዚሁ ስማቸውን የማናነሳው፣ መልካቸውንም የማናውቀው ጀግኖች ናቸው። ስለዚህ ውለታ-ቢስነት ክንፉን ዘርግቶ ሳይንሰራራብን በስም-የለሾች ህይወት ተረማምደን አንድ እርከን ወደ ላይ ከፍ ባልን ቁጥር "ስም-የለሾች"ን ልናውቅና ስም-ልንሰጣቸው ይገባል። ለህሊና ወይም ለፈጣሪ ስንል አዎ ምስጋና ለስም- የለሽ!

*ህዳር ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*